## የቻይልድ ፋይንድ ተልዕኮ መግለጫ

የኤሲፒኤስ ቻይልድ ፋይንድ ፈልግ አስፈላጊነት የእድገት ዝግመት ወይም ጉዳት እንዳለባቸው የሚጠረጠሩ ህጻናትን አፈላልጎ ማግኘት እና ምዘና ማድረግ ነው:: ህጻኑ/ኗ ያለበት ጉዳት ትምህርቱ/ቷ ላይ ጣልቃ የሚገባ ከሆነ የመጀመሪ ህጻንነት ደረጃ ልዩ ትምህርት(ኢ. ሲ. ኤስ ኢ.) እና/ወይም ሌሎች ተጨማሪ አገልግሎቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ሌሎች አገልግሎቶች ሊያካትቱት የሚችሉት፣ በዚህ ብቻ ባይወሰኑም፣ የንግግር/ የቋንቋ ህክምና፣ አካላዊ ህክምና ወይም የሙያ ተኮር ህክምና ናቸው::



## አንድን ህጻን ማን መጠቆም ይችላል?

አንድን ህጻን ለኤሲፒኤስ ቻይልድ ፋይንድ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት በማናቸውም ሰዎች ሊጠቆም ይችላል

- ወላጅ/ ሞግዚት
- የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ
- የጤና ባለሞያ
- የትምህርት ቤት ሰራተኞች
- የህጻናት እንክብካቤ ሰጪ አካል
- የማህበረሰብ ተወካይ
- የጨቅላ ሚድህ ግንኙነት - የወላጅ - ህጻናት ትምህርት (አይ ቲ ሲ -ፒ አይ ኢ.) ሰራተኛ

**ለ ኤሲፒኤስ ተጨማሪ ስራዎች የቤተሰብ/ ሞግዚት ተሳትፎ አስፈላጊ ነው::**



## ተጨማሪ ግብዐቶች

- የቨርጂኒያ የመጀመሪ ህጻንነት ደረጃ ትምህርት ክፍል www.VDOE.verginia.gov/spedal ed/ early childhood
- የልዩ ትምህርት የወላጆች መመሪያ የቨርጂኒያ ትምህርት ክፍል http://www.doe.verginia.gov/special-ed/parents/parents_guide.pdf
- የጨቅላ ሚድህ ግንኙነት - የወላጅ - ህጻናት ትምህርት (አይ ቲ ሲ-ፒ አይ ኢ). (እድሜያቸው ከ 0 እስከ 3) www.infantva.org 703-746-3350
- የኤሲፒኤስ ት/ቤት ማውጫ ( ለትምህርት እድሜ 5 እስከ 22) www.acps.k12.va.us/schools.php 703 -619-8000

### ኤሲፒኤስ ቻይልድ ፋይንድ

ለበለጠ መረጃ እባክዎ በዚህ ያግኙን:

703-578-8217

childfind@acps.k12.va.us

ቻይልድ ፋይንድ

እና

የመጀመሪያ ህጻንነት ደረጃ ልዩ ትምህርት አገልግሎት

ጄፈርሰን- ሂውስተን ት/ቤት

1501 Cameron Street, Suite 235
Alexandria, VA 22314

# ACPS
Alexandria City Public Schools

## ቻይልድ ፋይንድ እና የመጀመሪያ ህጻንነት ደረጃ ልዩ ትምህርት አገልግሎት

### ሁሉም ተማሪ ይሳካለታል

CHILD Find

## ስለልጆ እድገት ያሎትን ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት እንረዳዎታለን:

ኤሲፒኤስ ቻይልድ ፋይንድ ላለንበት የትምህርት ዘመን መስከረም ላይ እድሜያቸው ሁለት አመት ለሆናቸው ህጻናት፣ እስከ አምስት አመታቸው ድረስ የእድገት ዝግመት አለባቸው ተብለው ለተጠረጠሩ፣ ወይም የመማር ወይም ትምህርት የመቀበል አቅሙን/ሟን ሊያጠቃ የሚችል ጉዳት ላለባቸው ህጻናት ነፃ ምርመራና/ ወይም ምዘና ይሰጣል::

## መመራት

ኤሲፒኤስ ቻይልድ ፋይንድ እድሜቸው ከ ሁለት እስከ አምስት ላሉ የእድገት ዝግመት ወይም ጉዳት አለባቸው ተብለው ለሚጠረጠሩ ህጻናት ነፃ የምርመራና/ወይም



### አንድ ህጻን መቼ ወደ ቻይልድ ፋይንድ ሊመራ ይገባዋል?

- አንድ ህጻን ( የመግባባት፣ አካላዊ፣ የማሰብ/ምክኒያታዊነት፣ ራስን መርዳት እና/ወይም ግላዊ - ማህበራዊ) የእድገት ምዕራፎችን ሳያሟላ ሲቀር
- ወላጅ/ አሳዳጊ ፣ወይም ከቤተሰብ ውጭ ያለ ሰው፣ ልጁ የሚለውን መረዳት ሲያቅተው ወይም ልጁ ለመግባባት/ ለመናገር ሲያቅተው
- የአካላዊ ሁኔታ ወይም የጤና መዛባት በልጁ እድገት እና/ ወይም ማወቅ ላይ ጣልቃ ሲገባ

አስተውሉ፡ ልጆች የግድ ሁሉንም ባይሆን ተመሳሳይ የሆኑ ባህሪዎች ሊያሳዩ ይችላሉ:: ማንኛውም የልጁን የማወቅ አቅሙን የሚያውክ ሁኔታ ለመታየት መሰረት ሊሆን ይችላል::

ጥርጣሪያችን ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ ብቻ ሊገደብ አይገባውም::

## መመርመር

### የምርመራ ቀጠሮ ወቅት ምን እንጠብቅ?

ወላጅ/አሳዳጊ ከቻይልድ ፋይንድ ሰራተኛ ጋር ስለ ልጁ እድገት መወያየት

ልጁ የሚመረመረው በእድገቱ ዙሪያ በመጀመሪያ ህጻንነት ደረጃ ልዩ ትምህርት አስተማሪ ነው

- የመግባባት ክህሎቶች
- የምክንያታዊነት/ የማሰብ ክህሎቶች
- እራስን የመርዳት/ የመላመድ ክህሎቶች
- የግል - ማህበራዊ ክህሎቶች
- የአዕምሮ - ነርቭ ቅንጅት ክህሎት

ሰራተኛው የምርመራውን ውጤት ከወላጅ/ አሳዳጊ ጋር ይመለከትና ልጁን/ቷን በትምህርቱ/ ቷ ለመደገፍ መወሰድ ያለበት ማንኛውም ቀጣይ እርምጃ ላይ ይወያያሉ

የሚከተሉት ሰነዶች መሟላት ይኖርባቸዋል:

- የአሌክሳንድሪያ ነዋሪነት ማስረጃ(ሁለት ቅጾች)
- የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ዋናው
- የወላጅ/ አሳዳጊ መታወቂያ (የመንጃ ፈቃድ ወይም ፓስፖርት) ወይመ ህጋዊ የማሳደግ ሃላፊነት ወይም ሞግዚትነት፣ የሚመለከትዎት ከሆነ




**እንዴት መጀመር ይቻላል**

**ቻይልድ ፋይንድን በዚህ ያግኙ 703-578-8217**

## ሂደቱ

በልጅዎ ምርመራ ውጤት መሰረት ተጨማሪ ምዘና ወይም ጣልቃ መግባት አስፈላጊ ለመሆኑ ኤሲፒኤስ የክትትል ቀጠሮ ሊያዝ ይችላል::

**የመጀመሪያ ደረጃ፡** ልጁን የማጥኛ ቀጠሮ

- ቡድኑ የልጁን ጥንካሬና ፍላጎት ወላጅ ባለበት ይመለከታል
- የተጨማሪ ምዘና ወይም ምልከታ አስፈላጊነትን ለመወሰን
- ለተጨማሪ ምዘና የቤተሰብ ፍቃድ ያ ስፈልጋል

**ሁለተናው ደረጃ፡** የምዘና ቀጠሮ(ዎች)

- በሚጠረጠረው ጉዳት አካባቢ(ዎች) ምዘና ይካሄዳል

**ሦስተኛው ደረጃ፡** ብቁነት ማረጋገጫ ቀጠሮ

(ከተመራበት በ65 የስራ ቀናት ውስጥ)

- ቡድኑ ወላጅ ባለበት የምዘናዎቹን ውጤት ይመለከታል
- በተተረጠሩ የጉዳቱ አካባቢዎች የብቁነቱን መመዘኛ ይመለከታሉ

**አራተኛው ደረጃ፡** መመዘኛውን ካሟላ ግለሰብ ተኮር የማስተማሪያ ቀጠሮ (መመዘኛውን መሟላቱ ከታወቀ በ 30 ቀናት ውስጥ)

- ቡድኑ የልጁን ጥንካሬና ፍላጎት ወላጅ ባለበት ይመለከታል
- በአይ ኢፒ ቡድን የተዘጋጀ አመታዊ ግቦችን መመልከት
- አገልግሎቱን መቃኘት
- አገልግሎቱን ለመተግበር የቤተሰብ በጎ ፍቃድ የስፈልጋል